# የስብሰባ ጥሪ

## ለንስር ማይክሮፋይናንስ ኢንስቲትዩሽን አክሲዮን ማኅበር ባለአክስዮኖች በሙሉ

የንስር ማይክሮፋይናንስ ኢንስቲትዩሽን አ.ማ. ባለአክሲዮኖች 11ኛ መደበኛ ጠቅላላ ጉባዔ ቅዳሜ፤ ህዳር 28 ቀን 2017 ዓ.ም. ከቀኑ 9:00 ሰዓት ጀምሮ በአዲስ አበባ ከተማ ኃይሌ ግራንድ ሆቴል ይካሄዳል፡፡ ስለሆነም የአክስዮን ማኅበሩ ባለአክሲዮኖች በተጠቀሰው ቀንና ቦታ እንድትገኙ የዳይሬክተሮች ቦርድ ጥሪውን በአክብሮት ያስተላልፋል፡፡

### 1. ማኅበሩን የሚመለከቱ ዋና ዋና መረጃዎች

| | |
|---|---|
| 1.1 የአክስዮን ማኅበሩ ስም | ንስር ማይክሮፋይናንስ ኢንስቲትዩሽን አ.ማ. |
| 1.2 የአክስዮን ማኅበሩ ዓይነት | በአነስተኛ የፋይናንስ ሥራ ላይ የተሰማራ |
| 1.3 የአክስዮን ማኅበሩ የተፈረመ ዋና ገንዘብ | ብር 482,101,526.24 |
| 1.4 የአክስዮን ማኅበሩ የተከፈለ ዋና ገንዘብ | ብር 482,101,526.24 |
| 1.5 የአክስዮን ማኅበሩ የምዝገባ ቁጥር | MT/AA/3/0026952/2006 |
| 1.6 የአክስዮን ማኅበሩ ዋና መስሪያ ቤት አድራሻ | አዲስ አበባ፤ ቦሌ ክ/ከ ፤ ወረዳ 03፤ የቤት ቁ.084 |

### 2. የ11ኛ መደበኛ ጠቅላላ ጉባዔ አጀንዳዎች

2.1 የጉባዔውን አጀንዳዎች ማፅደቅ፤

2.2 አዳዲስ ባለአክሲዮኖችን መቀበል እና የአክሲዮኖችን ግዢ እና ዝውውሮች ማፅደቅ፤

2.3 የዳይሬክተሮች ቦርድ ዓመታዊ ሪፖርትን ማዳመጥና ተወያይቶ ማፅደቅ፤

2.4 የውጭ ኦዲተሮች ዓመታዊ ሪፖርትን ማዳመጥና ተወያይቶ ማፅደቅ፤

2.5 እ.ኤ.አ የ2023/2024 በጀት ዓመት የትርፍ አደላደል እና አከፋፈል ላይ የቀረበውን የውሳኔ ሃሳብ ተወያይቶ ማፅደቅ፤

2.6 የውጭ ኦዲተር ሹመት እና ክፍያ ማፅደቅ፤

2.7 የጉባዔውን ቃለ ጉባኤ በንባብ ማሰማትና ማፅደቅ፤

### 3. ማሳሰቢያ

3.1 ማንኛውም ባለአክሲዮን በስብሰባው ላይ ለመገኘት ማንነቱን እና ኢትዮጵያዊ ወይም ትውልደ ኢትዮጵያዊ መሆኑን የሚያሳይ የታደሰ መታወቂያ ወይም ፓስፖርት ይዞ መቅረብ አለበት፡፡

3.2 ውል ለማዋዋል ህጋዊ ሥልጣን በተሰጠው አካል የተረጋገጠና በስብሰባ ላይ ለመካፈል እና ድምፅ ለመስጠት የሚያስችል ውክልና ያለው የባለአክሲዮን ተወካይ የውክልና ሥልጣን ማስረጃውን ዋናውንና ኮፒውን ይዞ መቅረብ አለበት፡፡

3.3 በአካል መገኘት የማይችሉ ባለአክሲዮኖች ከስብሰባው 3 /ሦስት/ የሥራ ቀናት በፊት ቦሌ ሩዋንዳ አከባቢ በሚገኘው የማኅበሩ ዋና መስሪያ ቤት ህንጻ 5ኛ ፎቅ ላይ በሚገኘው የማኅበሩ የአክሲዮን ክፍል በመቅረብ የውክልና መስጫ ቅፅ መሙላት ይችላሉ፡፡

3.4 የአክሲዮን ማኅበሩን የቦርድ አባላት እና ሰራተኞች መወከል አይቻልም፡፡ አንድ ባለአክሲዮን መወከል የሚችለው አንድ ተወካይ ብቻ ነው፡፡

3.5 ባለአክሲዮኖች በስልክ ቁጥር 0115 622225/0115 622668 በመደወል ተጨማሪ መረጃዎችን ማግኘት ይችላሉ፡ :

**የንስር ማይክሮፋይናንስ ኢንስቲትዩሽን አ.ማ የዳይሬክተሮች ቦርድ**